ግልጽ ደብዳቤ ለአቶ መለስ ዜናዊ

<u>አዲስ አበባ</u>

ከምህረቱ ዘቀጨኔ

የሰላም ሰላምታዬ ይድረስዎ።

እ.ኤ.አ. በ02/04/2010 ዓ. ም. በአይጋ ፎረም ድረ-ገጽ ላይ "ከመራራ ዛፍ፣ ጣፋጭ ፍሬ አይለቀምም" በሚል ርዕስ ዕንቁ ስላሴ ወልዱ በሚል የብዕር ስምዎ የፃፉትን አሳፋሪ ፅሑፍ በትዝብት አነበብኩት። በብዕር ስምዎ ያልኩት በዘፈቀደ አይደለም። በፅሑፉ ስልት፣ በቋንቋው ፍሰት፣ በሃይለ-ቃሉ ትምክህተኝነት የርስዎ ለመሆኑ በግልጽ ይታወቃል። ያለዚያማ እንዲህ ያለ በሙሉ ስልጣንና በማን አለብኝነት የሚሰነዘር ፅሑፍ ከየትኛው ዓለም የበቀለ ዕንቁ ስላሴ ወልዱ የሚባል ግለሰብ ሊፅፍ ይችላል?! ፅሑፉ የራስዎ ለመሆኑ ማስተባበል አይቻልም።

እኔ ግን ይህን ደብዳቤ እንዲፅፍ ያስገደደኝ አሁንም ከአለፈው የማይማረው ሰብአዊ ባህሪዎ አልገባኝ ስላለ ነው። "ነፃ ምርጫ" ይካሄዳል ተብሎ ደፋ ቀና በምትሉበት ወቅት፣ የዚያችን ምስኪን የብርቱካንን ጉዳይ አንተርሰው ይህን ያህል ያዙኝ ልቀቁኝና ማስፈራራት ምን አመጣው? በለስ ቀንቶዎ "ሁሉንም ምን አባታችሁ ትሆናላችሁ!" ብለው እንደፈለግዎ መፍለጥ መቁረጥ የዕለት ስራዎ ከሆነ 18 ዓመታት አልፈዋል።

በአምባገነንነት ምርጫውን ተከትሎ ለማሰርዎ ዕውቅና ሰጥተዋቸው የነበሩትን ጥቂት መሪዎችና ጋዜጠኞች ሲፈቷቸው፣ አሁንም ባይጠቅሱትም በረቀቀ የሽምግልና ዘዴ የለቀቋቸው ተቃዋሚዎች ከወ/ት ብርቱካንና ከዶ/ር ብርሃኑ በስተቀር ይኸው አቅማቸውን አውቀው እርስዎ በመረጡት የጨዋታ ሕግና በርስዎ የመስክ ክልል ለመጫዎት ያንኑ የየዋህነት ወይም የማጀብ ልምምዳቸውን እያደረጉ ነው። በሺህዎች የሚቆጠሩት የብርሸለቆ፣ የዴዴሳ፣ የዝዋይ፣ የሸዋ ሮቢትና የሌሎቹ የሚታወቁም ሆኑ የድብቅ እስር ቤቶች የፖለቲካ እስረኛዎች አሁንም እየማቀቁ ይገኛል። ታዲያ ይህን ያህል ማስፈራራት ምን አስፈለግዎ? ልብ ይበሉ! አንዳንዶቹ ዳር ዳር እንደሚሉት፣ እንደውም ከዚህ በየጊዜው ወፈፍ ከሚያደርገው ሰው ጋር አንጫዎትም ቢሉዎ ብቻዎን ሲሮጡ ውለው፣ አሸነፍኩ ለማለት ነው? ከየዋሃኑ ወይም ከአጃቢ አሯሯጮችዎ የተወሰኑት በድንገት ጎራቸውን ከሕዝብ አድርገው ጨዋታው ፈረሰ ቢሉዎት ማለቴ ነው። ሐሞታቸው መረር ቢል ማለቴ ነው። ለነገሩማ ተማሪውን፣ መምህሩን፣ ገበሬውን፣ ወታደሩን፣ ነጋዴውን፣ የመንግስት ሰራተኛውንና የየዕምነት መሪዎችን ሳይቀር በፈላጭ ቆራጭ ስልጣንዎ ጡንቻ ማስፈራሪያነት በየዘርፉ አደራጅተው እንደጨረሱ ደጋግመው ተናግረዋል። ግን አንድ ቁም ነገር ላስታውሰዎ። ስንቱ ለምዝገባ ቀርቧል? እንደሚመርጥዎ ምን ያህል እርግጠኛ ነዎት? መቼም ጨዋታውን ብቻዎትን ከጀመሩት ይኸ ሁሉ ውስጥ ውስጡን በማን እንደሚስቅ ሊገነዘቡት ይገባል። እንደማንኛውም አምባገነን እራስዎትን ያታልሉ እንጂ፣ ህዝቡማ ደርግ ምርጫ ብሎ፣ የኢሰፓን ዋና ዋና አጋፋሪዎች የዝሆን የምርጫ ምልክት እያሸከመ ከሁለት ሁለት አጃቢዎች ጋር በማቀናጀት በየቀበሌው ምርጫ ሲል፡

አንበሳውም ሞተ፣ ጎሹም ፈረጠጠ፣
ዝሆን ሊገዛን ነው፣ በእግሩ እየረገጠ

እንዳለው፣ አሁንም የባለቅኔው የገሞራው ስንኞችን መነሻ በማድረግ፡

ካምስት ዓመት በፊት በንብ ተመስላ፣
ያች ያየናት ዝንብ፣ ህፃናት ስትበላ፣
ደም እያፈሰሰች፣ የምሷን ልታድርስ፣
አሁንም ውድድር፣ ምርጫ ብትደግስ፣
በድርጅት ይሁን፣ በግልም ተባለ፣
አሸናፊ የለም፣ ሕወሓት እስካለ።

በማለት ይሳለቅበዎታል። የሚያጨበጭብልዎ ሁሉ ደጋፊዎ እንዳልሆነ ልበዎ ይረዳዋል መቼም። በአሁኑ ጊዜ ሁሉም አቅምና መድረክ አጥቶ እንጂ በደል ተሸክሞ፣ ውስጡ እያረረ የተቀመጠ ህዝብ ነው። ጌቶችዎም ቢሆኑ ይህን ያህል ደክመው፣ አጃቢወችዎን እየኮረኮሙ አዋዝተውልዎ፣ ብቻዎን ለመጫዎት መሮጥ ሲጀምሩ፣ እንደለየለዎት አውቀው፣ መሳቂያ ብቻ ሳይሆን ማፈሪያ በመሆንዎ ማዘናቸው አይቀርም። ለእርስዎ የሚበጅዎ ከነዚህ እራሳቸውን ከሚያታልሉ የዋሆች ወይም ታዛዥ አጃቢወችዎ ጋር በራስዎ ደንብ ቢጫወቱ ነው።

ለመሆኑ “ብርቱካን አትፈታም!” የሚሉት በሰማይም፣ በምድሩም የሚያዙ እርስዎ ነዎትን?! “እግረ ቀጭን ይሞታል ሲባል፣ እግረ ወፍራም ይሞታል” ይባላል። ይህችን ተረት እንዳይረሷት። እርስዎና ዘመናይቷ ባለቤትዎ ልጆች እንዳሏችሁ፣ ለቅጽበትም እንኳ መዘንጋት አይገባችሁም። ሃሌ አይቀልድባትም! አምላክ አላት፣ ሕዝብ ይደግፋታል። ሕዝቡን ጨርሶ መናቅ የለየለት የዕብደት ዋዜማ ነው። እራስዎን ይመርምሩ። ስንት ዓመት ሊኖሩ ነው?!